

# Public Hearing Notice B12-01 & B12-02 AM

# የሕዝብ ችሎት ማስታወቂ

**የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን**

## ሰነድ B12-01: ለ2013 ዓ.ም. የታቀደ የዋጋ ለውጥ እና

## ሰነድ B12-02: ለ2013 ዓ.ም. የታቀደ የሀብት ማሻሻል ፕሮግራም እና የፌደራል የ2012 ዓ.ም. የእርዳታ መጠየቂያ ማመልከቻዎች

**<u>ዓላማ</u>**

**የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ሰነዶች በተመለከተ ስድስት የሕዝብ ችሎት ስብሰባዎች ከታች በተዘረዘረው መሠረት እንደሚያካሂድ ያስታውቃል።**

የችሎት ቁጥር 569
<u>ሰኞ, የካቲት 27, 2012</u>
የቤተሲዳ ቼቪቼዝ
አካባቢ አገልግሎት ማዕከል
4805 Edgemoor Ln
Bethesda, MD

የችሎት ቁጥር 570
<u>እሮብ, የካቲት 29, 2012</u>
ሜሪ ኤለን ሄንደርሰን
መካከለኛ ትምህርት ቤት ካፌቴርያ
7130 Leesburg Pike
Falls Church, VA

የችሎት ቁጥር 571
<u>ሀሙስ, መጋቢት 1, 2012</u>
የማቲዎስ መታሰቢያ ባብቲስት
ቤተክርስቲያን
ጆን ኤች ከርኒ
የመሰብሰቢያ አዳራሽ
2616 Martin Luther King Jr Ave, SE
Washington, DC

የችሎት ቁጥር 572
<u>ሰኞ፣ መጋቢት 5, 2012</u>
ዋሽንግተን ሊ ሁለተኛ ደረጃ
ት/ቤት ካፌቴርያ
1301 N Stafford St
Arlington, VA

የችሎት ቁጥር 573
<u>ማክሰኞ፣ መጋቢት 6, 2012</u>
ሴንት ኮሉምባ ኤፒስኮፓል
ቤተክርስቲያን
4201 Albemarle St, NW
Washington, DC

የችሎት ቁጥር 574
<u>እሮብ, መጋቢት 7, 2012</u>
ፈርስት ዩናይትደ ሜዘዲስት
ቤተክርስቲያን
6201 Belcrest Rd
Hyattsville, MD

ለእያንዳንዱ ቦታ: ክፍት ሸንጎ በ6 p.m. — የሕዝብ መደመጥ ሸንጎ በ7 p.m.

**እባክዎ ቀኖቹ የዓየር ለውጥ ከኖረ በእያንዳንዱ ድርጅት የዓየር ለውጥ የህንፃ መዘጋት ፖሊሲ መሠረት ሊለወጥ እንደሚችል ይገንዘቡ።**

የሕዝብ የመደመጥ ቦታዎች በሙሉ የተለየ እርዳታ እንደ የምልክት ቋንቋ፣ የትርጉም አገልግሎት ወይም በስብሰባው ለመካፈል ተጨማሪ እርዳታ ለሚፈልግ ለማንኛውም ግለሰብ አስፈላጊው ዝግጅት እንዲደርግ ዳኒስ ፒናን በስልክ ቁጥር 202-962-2511 ወይም TTY: 202-638-3780 መደወል አለባቸው። የቋንቋ ማለትም እንደ አስተርጓሚ የመሳሰለ እርዳታ ካስፈለገ በ202-962-1[illegible]2 ይደውሉ።

ስለ ችሎቱ የሚገልጹ መረጃዎች በአካባቢው በሚገኙ መፀሐፍት ቤቶች፣ አውቶቡሶች፣ ሜትሮ ማመላለሻዎች እና በድረ ገጽ www.wmata.com/hearings ይሰራጫሉ።

**ተናጋሪ ለመሆን እንዴት እንደሚመዘገቡ** – እነኝህን ሁለት ሰነዶች በተመለከተ ለመናገር የሚፈልጉ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ሀሳባቸውን ለመሰንዘርና የድጋፍ ቃላቸውንና አማራጭ ሀሳብ ለመስጠት ዕድል ይሰጣቸዋል። የምስክሮች ዝርዝር ለማዘጋጀት እንዲረዳን በነዚህ የሕዝብ ችሎቶች ለመናገር የሚፈልጉ ግለሰቦችና የድርጅት ተወካዮች ስማቸውንና የድርጅት ተወካይ ከሆኑ የድርጅታቸውን ስም፣ በኢ-ሜል speak@wmata.com ወይም በሚከተለው አድራሻ በፖስታ ቤት መላክ አለባቸው - Office of the Secretary, Washington Metropolitan Area Transit Authority, 600 Fifth Street, NW, Washington, D.C. 20001. ወይም በፋክስ ቁጥር 202-962-1133 መላክ ይችላሉ። እባካችሁ በእያንደንዱ ደብዳቤ የአንድ ተናጋሪ ሰው ስም ብቻ ላኩ። የእያንዳንዱ ተናጋሪዎች ዝርዝሮች ተቀባይነት የላቸውም። ይህ ዝርዝር በዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን ሬከርዶችን ለሕዝብ ይፋ የማድረግ ፖሊስ መሠረት ለሕዝብ ይፋ ሊደረግ እንደሚችል ይወቁ። ፖሊሲው በዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን ድረ ገጽ wmata.com/about_metro/public_rr.cfm "የህግ ጉዳዮች" በሚለው ሥር ይገኛል። በመጀመሪያ የሕዝብ ባለሥልጣኖች ለአምስት ደቂቃ ይናገራሉ። ሌሎች ተናጋሪዎች ሶስት ደቂቃ ብቻ ይፈቀድላቸዋል። ተናጋሪው በአንዱ ወይም በሁለቱም ሰነዶች ላይ ቢናገርም የሶስት ደቂቃው ገደብ አይለወጥም። የጊዜ ገደቡን አንዱ ተናጋሪ ለሌላ ማስተላለፍ አይቻልም።

**የተጻፉ መግለጫዎች እንዴት እንደሚቀርቡ** – የጽሁፍ መግለጫዎችና መረጃዎቹ ሰኞ መጋቢት 12 ቀን 2012 ዓ.ም. ከምሽቱ አስራ አንድ ሰዓት በፊት ለፀኃፊው ቢሮ መድረስ አለበት፣ በኢ-ሜል writtentestimony@wmata.com መላክ ይቻላል። እንዲሁም በሚከተለው አድራሻ - Office of the Secretary, Washington Metropolitan Area Transit Authority, 600 Fifth Street, NW, Washington, D.C. 20001 በፖስታ ቤት መላክ ይቻላል። ወይም በፋክስ ቁጥር 202-962-1133 መላክ ይቻላል። እባክዎ ሲልኩ የሰነድ ቁጥር (B12-01 እና/ወይም B12-02) ይጨምሩበት። የተሰጡት የግል መረጃዎች፣ እንደ ስም፣ ኢ-ሜል አድራሻ፣ የቤት አድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር በዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን ሬከርዶችን ለሕዝብ ይፋ የማድረግ ፖሊስ መሠረት ለሕዝብ ይፋ ሊደረግ እንደሚችል ይወቁ።

**ጥናትና ክፍት ስብሰባ** – በተጨማሪም የሜትሮ በጀትን ስለማስተካከል ጉዳይ በሚደረገው ጥናት ለመካፈል ከፈለጉ እባክዎ በድረ ገጽ www.wmata.com ይመልከቱ። ጥናቱ እአአ የካቲት 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ከምሽቱ አስራ አንድ ሰዓት ጀምሮ መጋቢት 12 ቀን 2012 ዓ.ም. ከምሽቱ አስራ አንድ ሰዓት ይዘጋል። ሜትሮ በጀቱን እንዴት ማስተካከል እንደሚችልና አንዳንድ የዴሞግራፊ ነክ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይጠየቃሉ። ይህ አማራጭ በሕዝብ ችሎት ከመናገርና የጽሁፍ መግለጫ ከማቅረብ በተጨማሪ የሚደረግ ነው። የጥናቱ ውጤት ለሜትሮ የቦርድ ዳይሬክተሮች የሚቀርብ ሲሆን የችሎቱ ኦፊሴል ሰነድ ውስጥ አይካተትም።

ከእያንዳንዱ የሕዝብ ችሎት በፊት፣ በዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን ለ2013 ዓ.ም. የቀረበውን በጀት እና ክፍያ እንዲሁም የ2013 ዓ.ም. የንብረት መሻሻል ፕላንን በተመለከተ ሕብረተሰቡን ለማሳተፍና ከሕዝቡ ሀሳብ ለመስማት ሜትሮ ክፍት የሆነ የአንድ ሰዓት ሸንጎ ያካሂዳል።. ሜትሮን ለማሳደስ ያለውን እንቅስቃሴ እና አሁን የተደረሰበትን ውጤት እንዲሁም የታቀደውን በጀት ዋና ክፍሎች በተመለከተ የሚያሳይ ቪዲዮ በተከታታይ በአንዱ ጣቢያ ይታያል። በሌላ በኩል ነባር የአውቶቡስ፣ ሜትሮ አክሰስ፣ የሀዲድ፣ ስማርት ትሪፕ እና የፖሊስ ባለሥልጣኖች በጠረቤዛ አካባቢ በመቀመጥ ከተሳታፊዎች የሚቀርቡ የግል ጥያቄዎችን

ይመልሳሉ። እንዲሁም የቀጣሪ ክፍል ጠረቤዛ በእያንዳንዱ የሸንጎ ዝግጅት ክፍል ይኖራል። ሶስተኛ ጣቢያ “ሳይበር ካፌ” ክፍለ ጊዜ የሜትሮን የተስተካከለ በጀት እና የቀረበውን ክፍያ በተመለከተ ተካፋዮች በኦንላይን ጥናት መካፈልና የጽሁፍ መረጃ ለሬከርዱ ለማስገባት ያስችላሉ።

የጥናቱ ውጤት እና በሸንጎ ክፈለ ጊዜ የሚሰነዘሩት ሀሳቦች ለሜትሮ የቦርድ ዳይሬክተሮች የሚቀርቡ ሲሆን የችሎቱ ኦፊሴል ሰነድ ውስጥ አይካተቱም።

**የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን የሰነድ B12-01 ዕቅድ: የ2013 ዓ.ም. የክፍያ ማስተካከያዎች ዕቅድ**

የታቀደው የመጭው ዓመት የሜትሮ የሥራና የንብረት በጀት አሳሳቢ የሆነውን የማደስ፣ ደህንነትንና አስተማማኝነት ይደግፋል። በተጨማሪም በጀቱ አገልግሎትን ለማዳበር በተለይም የሲልቨር መስመር መከፈትን አስመልክቶ ከሥራ በመግቢያና በመውጫ አጣዳፊ ሰዓቶች ጊዜ ተጨማሪ አገልግሎቶችን መጨመር፣ የኤስኬሌተሮች ጥገና፣ የአውቶቡስ ማቆሚያዎችን ኮሪዶር ማሻሻል እና የበለጠ የደህንነት አገልግሎቶችን መስጠትን ያካትታል። በተጨማሪም ሜትሮ የተዳከመውን የአሠራር ፕሮግራም ለማሻሻል እና የብሔራዊ የትራንስፖርት ደህንነት ቦርድ የሰጠውን አስተያየት ለመፈጸም ጥረቱን ይቀጥላል።

በአሠራር በኩል፣የ$1.6 ቢሊዮን የ2013 ዓ.ም. በጀት ካለፈው ዓመት የተጣራ የ$116 ሚሊዮን የወጭ ጭማሪ እና የ$3 ሚሊዮን የገቢ ቅናሽ ያሳያል። ይኽም ሲሆን የቻለው ወጭውን በአካባቢው ባለሥልጣኖች በመከፋፈል እና በተጠቃሚዎች ላይ ዋጋ በመጨመር ነው። የሚያካትተውም የታቀደው ከአካባቢው ባለሥልጣኖች $53 ሚሊዮን (8%) ጭማሪ እና የ$66 ሚሊዮን የባቡር መሳፈሪያ፣ የሜትሮ አክሰስ፣ የአውቶቡስ እና የመኪና ማቆሚያ ዋጋ ጭማሪ ነው። የታቀደው ማካካሻ የሚያካትተው - ትራፊክ በሚበዛበት ጊዜ ስማርት ትሪፕ ተጠቅሞ የባቡር መሳፈሪያ ዋጋዎች ላይ አማካይ የ5% ጭማሪ በማድረግ፣ እጅግ በጣም ትራፊክ በሚበዛበት ጊዜ የሚሰጠውን ቅናሽ በመቀነስ እና የአውቶቡስ መሳፈሪያ ዋጋ ላይ የ$0.10 ጭማሪ በማድረግ ነው።

ከ$116 ሚሊዮን ተጨማሪ በጀት $61 ሚሊዮኑ አሁን ላሉ እንቅስቃሴዎች ተጨማሪ ወጭዎች ላይ ይውላል: ከግማሽ በላይ ተጨማሪ ወጭዎች የመጡት ከጥቅማ ጥቅሞች በተለይም የጤና ጥቅማ ጥቅሞች እና $29 ሚሊዮን ተጨማሪ የጡረታ ጥቅሞች ሲሆን ሌላው አጋማሽ የኮንትራት ሠራቶኞች መጨመር እና ተጨማሪ ከሠራተኛ ጋር ያልተያያዙ ወጨዎች ምክንያት ነው። ቀሪው $55 ሚሊዮን ለደህንነት፣ ፀጥታ፣ አስተማመኝ ለሆኑ ሌሎች የማሻሻያ ፕሮግራሞችህ ላይ ይውላል።

የታቀደው የመሳፈሪያ መስተካከል ከከተማ ውጭ ለሚመጡ ተሳፋሪዎች እና ለማያዘወትሩ ተሳፋሪዎች አጠቃቀሙን ለማቃለል፣ የስማርት ትሪፕ አጠቃቀምን ለመገፋፋት እና በጥሬ ገንዘብ ክፍያ የአውቶቡስ መሳፈሪያ ጊዜን ለማሻሻል ነው።

በተለይም አስፈላጊውን $66 ሚልዮን ለመሰብሰብ ሜትሮ ከታች የተዘረዘሩትን የተለያዩ የክፍያ ለውጦችን እያቀደ ነው።

# መሳፈሪያ እና ክፍያዎች

| | የባቡር መሳፈሪያ | ወቅታዊ መሳፈሪያ/ክፍያዎች | የ2013 ዓ.ም. የታቀደ የክፍያ አማራጮች |
|---|---|---|---|
| | **ትራፊክ የሚበዛበት ጊዜ ክፍያ** | | |
| 1 | · የመሳፈሪያ ክፍያ | $1.95 | **$2.10** |
| 2 | · በ3 እና በ4 ማይልስ መሀከል የተቀኛጀ መስመር | $0.299 | **$0.316** |
| 3 | · ከስድስት ማይል በላይ የሆነ የተቀኛጀ መስመር | $0.265 | **$0.280** |
| 4 | ·የመጨረሻ ትራፊክ የሚበዛበት ጊዜ | $5.00 | **$5.75** |
| 5 | ወይም ·ከፍተኛ ትራፊክ የሚኖርበት ጊዜ አማራጭ | $5.00 | **$6.00** |
| 6 | · ለአዛውንቶችና/አካለስንኩሎች ትራፊክ በሚበዛበት ሰዓት ግማሽ ዋጋ | $0.95 - $2.50 | **$1.05 - $2.85** |
| 7 | · ወ/ለአዛውንቶችና/አካለስንኩሎች ትራፊክ በሚበዛበት ሰዓት ግማሽ ዋጋ አማራጭ | $0.95 - $2.50 | **$1.05 - $3.00** |
| 8 | ·ከፍተኛ ትራፊክ የሚኖርበት ጊዜ አማራጭ | $0.20 | **ይወገዳል** |
| | **ትራፊክ በማይበዛበት ጊዜ መሳፈሪያ** | | |
| 9 | · የመሳፈሪያ ዋጋ | $1.60 | **$1.70** |
| 10 | · በ3 እና በ4 ማይልስ መሀከል የተቀኛጀ መስመር | NA | **$0.237** |
| 11 | · ከስድስት ማይልስ በላይ የሆነ የተቀኛጀ መስመር | NA | **$0.210** |
| 12 | · የመጨረሻ ትራፊክ የሚበዛበት ጊዜ ክፍያ | $2.75 | **$3.50** |
| 13 | · ለአዛውንቶችና/አካለስንኩሎች ትራፊክ በሚበዛበት ሰዓት ግማሽ ዋጋ | $0.95 - $2.50 | **$1.05 - $3.00** |
| 14 | · ከሰባት ማይልስ በላይ የሆነ የተቀኛጀ መስመር ክፍያ | $1.60 | **ይወገዳል** |
| 15 | · በ7 እና በ10 ማይልስ መሀከል የተቀኛጀ መስመር ክፍያ | $2.15 | **ይወገዳል** |
| 16 | · ከ10 ማይልስ በላይ የሆነ የተቀኛጀ መስመር ክፍያ | $2.75 | **ይወገዳል** |
| | **ወይም ትራፊክ በማይኖርበት ጊዜ ክፍያዎች** | | |
| 17 | · የመሳፈሪያ ክፍያ | $1.60 | **$1.90** |
| 18 | · በ3 እና በ4 ማይልስ መሀከል የተቀኛጀ መስመር | NA | **$0.284** |
| 19 | · ከስድስት ማይልስ በላይ የሆነ የተቀኛጀ መስመር | NA | **$0.252** |
| 20 | · ·የመጨረሻ ትራፊክ የሚበዛበት ጊዜ ክፍያ | $2.75 | **$4.00** |
| 21 | · ለአዛውንቶችና/አካለስንኩሎች ትራፊክ በሚበዛበት ሰዓት ግማሽ ዋጋ | $0.95 - $2.50 | **$1.05 - $3.00** |
| | **በማግኔት ወረቀት መሳፈሪያ ዋጋዎች** | | |
| 22 | · ·የመጨረሻ ትራፊክ የሚበዛበት ጊዜ ክፍያ | NA | **$6.00** |
| 23 | · ትራፊክ በማይበዛበት ጊዜ ክፍያ | NA | **$4.00** |
| 24 | · ለአዛውንቶችና/አካለስንኩሎች ትራፊክ በሚበዛበት ሰዓት ግማሽ ዋጋ | NA | **$3.00** |
| 25 | · ከስማርት ትሪፕ ውጭ አማራጭ ክፍያ | $0.25 | **ይወገዳል** |
| | **ወይም - በማግኔት ወረቀት መሳፈሪያ አማራጭ ዋጋዎች** | | |
| 26 | · ከክልል ውጭ የወረቀት ካርድ ክፍያ (በእያንዳንዱ ክልል)) | NA | **$6.00** |
| 27 | · በዋና ክልል የወረቀት ካርድ ክፍያ (በእያንዳንዱ ክልል) | NA | **$4.00** |
| 28 | · ለአዛውንቶችና/አካለስንኩሎች ትራፊክ በሚበዛበት ሰዓት ግማሽ ዋጋ | NA | **$2.00-$3.00** |
| 29 | · ከስማርት ትሪፕ ውጭ አማራጭ ክፍያ | $0.25 | **ይወገዳል** |
| | **ወይም - በማግኔት ወረቀት መሳፈሪያ አማራጭ ዋጋዎች** | | |
| 30 | · ከስማርት ትሪፕ ውጭ አማራጭ ክፍያ | $0.25 | **$1.00** |
| 31 | · ለአዛውንቶችና/አካለስንኩሎች ትራፊክ በሚበዛበት ሰዓት ግማሽ ዋጋ | $0.10 | **$0.50 + 1/2 ትራፊክ በሚበዛበት ጊዜ** |

| | ሜትሮ፣ ይቀጥላል | ወቅታዊ<br>መሳፈሪያ /ዋጋዎች | **የ2013 ዕቅድ<br>የክፍያ አማራጮች** |
|---|---|---|---|
| | **የሀዲድ መተላለፊያ** | | |
| 32 | · የአንድ ቀን መሳፈሪያ, ከ9:30 a.m. በኋላ የሚያገለግል | $9.00 | **ይወገዳል** |
| 33 | · የአንድ ቀን መሳፈሪያ, የጊዜ ገደብ የሌለው | አይመለከተውም | **$14.00** |
| 34 | · የ7 ቀን የአጣዳፊ መሳፈሪያ - በስማርት ትሪፕ- ለሚያገለግሉ | $47.00 | **$57.50** |
| 35 | · የ28 ቀን አጣዳፊ መሳፈሪያ - በስማርት ትሪፕ- ለሚያገለግሉ | አይመለከተውም | **$230.00** |
| 36 | · የ7 ቀን የአጭር ጉዞ መሳፈሪያ | $32.35 | **ይወገዳል** |
| 37 | · ወይም የ7 ቀን የአጭር ጉዞ መሳፈሪያ በወረቀት መሳፈሪያ ካረድ ፋንታ | $32.35 | **$35.00** |
| 38 | · የ28 ቀን የአጭር ጉዞ መሳፈሪያ በወረቀት መሳፈሪያ ካርድ ፋንታ | አይመለከተውም | **$140.00** |
| | **ሌሎች የባቡር መሳፈሪያ ዋጋዎች** | | |
| 39 | · ስማርት ትሪፕ ተጠቅሞ ካውቶቡስ ወደ ባቡር መለወጥ | $0.50 ቅናሽ | ክፍያ የለውም |
| 40 | · የ30 ቀን የዲሲ የተማሪዎች ስማርት መሳፈሪያና በዲሲ የዲሲ ዋን ካርድ | $30.00 | **$32.00** |
| 41 | · የዲሲ የተማሪዎች መሳፈሪያ ካርድና የዲሲ ዋን ካርድ- በዲሲ የ10 ጊዜ መመላለሻ | $9.50 | **$10.00** |
| 42 | · በMARC እና በ VRE የመሸጋገሪያ ካርድ | $102.00 | **$108.00** |
| 43 | · በMTA የመሸጋገሪያ ካርድ | $157.00 | **$166.00** |
| | **የሜትሮ መሳፈሪያና ዋጋዎች** | | |
| | **የዘወትር መሳፈሪያዎች** | | |
| 44 | · ለአካባቢ/የተወሰነ ቦታ ለሚቆሙ አውቶቡሶች የስማርት ትሪፕ መሳፈሪያ ክፍያ | $1.50 | **$1.60** |
| 45 | ·ለፈጣን አውቶቡሶች የስማርት ትሪፕ መሳፈሪያ ክፍያ | $3.65 | **ክፍያ የለውም** |
| 46 | · ለአካባቢ/የተወሰነ ቦታ ለሚቆሙ አውቶቡሶች የጥሬ ገንዘብ ክፍያ | $1.70 | **$2.00** |
| 47 | ·ለፈጣን አውቶቡሶች በጥሬ ገንዘብ ክፍያ | $3.85 | **$4.00** |
| 48 | , ወደ ኤርፖ`ርት መንገድ ለሚሄዱ የካሽ/ ሰማርት ተሪፕ ክፍያ | $6.00 | **ክፍያ የለውም** |
| | **አዛውንቶች/አካለ ስንኩሎች: አንድ ሁለተኛ የተወሰነ መሳፈሪያ** | | |
| 49 | · ለአካባቢ/የተወሰነ ቦታ ለሚቆሙ አውቶቡሶች የስማርት ትሪፕ መሳፈሪያ ክፍያ | $0.75 | **$0.80** |
| 50 | · ·ለፈጣን አውቶቡሶች የስማርት ትሪፕ መሳፈሪያ ክፍያ | $1.80 | **ክፍያ የለውም** |
| 51 | · ለአካባቢ/የተወሰነ ቦታ ለሚቆሙ አውቶቡሶች በጥሬ ገንዘብ ክፍያ | $0.85 | **$1.00** |
| 52 | · ·ለፈጣን አውቶቡሶች በጥሬ ገንዘብ ክፍያ | $1.90 | **$2.00** |
| 53 | · ወደ ኤርፖ`ርት መንገድ ለሚሄዱ በጥሬ ገንዘብ/ስማርት ትሪፕ ክፍያ | $1.80 - $1.90 | **$3.00** |
| | **የአውቶቡስ ዝውውሮች** | | |
| 54 | · ሰማርት ትሪፕ ተጠቅሞ ከአዎቶቡስ ወደ አውቶቡስ መዘዋወር | $0.00 | **ክፍያ የለውም** |
| 55 | · ሰማርት ትሪፕ ተጠቅሞ ከባቡር ወደ አውቶቡስ መዘዋዋር | $0.50 ቅናሽ | **ክፍያ የለውም** |
| 56 | · ከMARC, VRE, እና MTA መዘዋወር | $0.00 | **ክፍያ የለውም** |
| 57 | · ከአካባቢ የሽርክና አውቶቡሶች መዘዋወሪያ | ይለያያል | **ክፍያ የለውም** |
| | የአውቶቡስ መሳፈሪያዎች | | |
| 58 | · የ7 ቀን የአካባቢ የአውቶቡስ መሳፈሪያ | $15.00 | **$16.00** |
| 59 | · የ7 ቀን የአካባቢ የአዛውንቶች/አካለስንኩሎች መሳፈሪያ | $7.50 | **$8.00** |
| | **Other Fare Media** | | |
| 60 | · 10 ቶክኖች በፓኬጅ ያለው ለድርጅቶች ይሰጣል | $17.00 | **$20.00** |
| 61 | · የዲሲ የተማሪዎች ቶክኖች - 10 ጉዞዎች በእያንዳነዱ ፓኬት | $7.50 | **$8.00** |
| 62 | · የዲሲ የተማሪዎች መሳፈሪያ በዲሲ ዋን ካርድ - 10 ጉዞዎች | $7.50 | **$8.00** |
| | **የሜትሮ አክሰስ መሳፈሪያዎች** | | |
| 63 | · የሜትሮ አክሰስ መሳፈሪያ (በADA 3/4 ማይልስ መተላለፊያ) | ይለያያል | ይለያያል |
| 64 | · ከፍተኛ ክፍያ | $7.00 | **$7.40** |

| | የመኪና ማቆሚያ ክፍያዎች | ወቅታዊ መሳፈሪያ/ዋጋዎች | የ2013 ዕቅድ የክፍያ አማራጮች |
|---|---|---|---|
| 65 | · የኮሎምቢያ ዲስትሪክት | $3.25 - $4.25 | **$3.50 - $4.50** |
| 66 | · የሞነትጎመሪ ካውንቲ | $4.00 - $4.75 | **$4.25 - $5.00** |
| 67 | · የፕሪንስ ጆርጅስ ካውንቲ | $4.25 | **$4.50** |
| 68 | · ቨርጂኒያ | $4.50 | **$4.75** |
| 69 | · ለወር የተከፈለበት የመኪና ማቆሚያ ክፍያ | $65.00 | **$45.00-$65.00** |
| 70 | · የመኪና ማቆሚያ ሜትሮች $1.00/60 ደቂቃዎች | $1.00 | **ክፍያ የለውም** |
| 71 | · የፕሪንስ ጆርጅስ የመኪና ማቆሚያ በኒው ካሮልተን | $85.00 | **ክፍያ የለውም** |
| 72 | · በሜትሮ ለማይሳፈሩ የመኪና ማቆሚያ ክፍያ | $8.25 - $25.00 | **ክፍያ የለውም** |
| | **ሌሎች ክፍያዎች** | | |
| 73 | · የቢስክሌት መቆለፊያ ኪራይ | $200.00 (በዓመት) | **$120.00 (በዓመት)** |
| 74 | · ለጣቢያው ማሻሻያ መግቢያ/መውጫ ተጨማሪ ዋጋ፣ ሁለት ጣቢያዎች በየባለሥልጣኑ | አይመለከተውም | **$0.05** |

የሕዝብ ችሎቶቹ በሚከተሉት የዋጋ ለውጥ ላይ የሕዝብ አስተያት ይጠይቃል: ሜትሮባስ፣ ሜትሮ ሬይል፣ ሜትሮአክሰስ፣ የመኪና ማቆሚያ እና ሌሎችም ዋጋዎች፡፡ የመሳፈሪያ ዋጋ ለውጥ በሥራ ላይ ለማዋል የታሰበው እአአ ሀምሌ 1, 2012 ዓ.ም. ወይም አካባቢ ነው፡፡ የ2013 ዓ.ም. የሥራ እና የንብረት በጀት ሙሉ ዝርዝር በድረ ገጽ www.wmata.com/about_metro/public_rr.cfm ይገኛል፡፡

## <u>የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን የሰነድ B12-01 ዕቅድ: የ2013 ዓ.ም. የንብረት ማሻሻያ ፕሮግራም እና የ2012 ዓ.ም. የዕርዳታ ማመልከቻዎች</u>

ሜትሮ መጀመሪያ ከተመሠረተበት ከ1970 ዓ.ም. ጀምሮ በ2011 ዓ.ም.  ሀይለኛ እና ከፍተኛ የሆነ የንብረት ፕሮግራም አካሂዷል፡፡ ድርጅቱ ባለፈው ዓመት ሀዲዶችን በማደስ፣ ኤስኬሌተሮችን በመጠገንና አውቶቡሶችንና ሜትሮአክሰ መኪናዎችን በመለወጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ ደህንነትን በተመለከተ ሜትሮ የብሔራዊ የትራንስፖርት ደህንነት ቦርድ ምክርን ሥራ ላይ ለማዋልና እና ሌሎችን አሳሳቢ የሆኑ የደህንነት ጉዳዮች ላይ ታላቅ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው፡፡

ሜትሮን ለመገንባት የታቀደው ወጭ የ2013 ዓ.ም. የንብረት በጀቱን እስከ ቢለዮን ዶላር እያደረሰው ነው፡፡ ከፌደራል መንግሥትና ከአካባቢው ባለሥለጣኖች፥- ሜሪላንድ፣ ቨርጅኒያ እና ዲስትሪከቱ ከሚገኘው ገንዘብ ከ90 በመቶ የሚሆነው በጀት በቀጥታ ለደህንነትና እምነት ለሚጣልበት አሠራር ላይ ይውላል፡፡

የ2013 ዓ.ም. የንብረት በጀት ምልከቶችን በማሻሻል፣ የሜትሮን አሮጌ ባቡሮችን - 1000-ተራ ቁጥር ባቡሮችን በአዲስ 7000-ተራ ቁጥር ባቡሮች በመተካት እና  ሃዲዶችን ማደስ እና በሌላ መተካት፣ ኤስኬሌተሮችንና ኤሊቬተሮችን በአዲስ በመተካትና ሌሎችንም ፕሮጀክቶችን በማካሄድ የብሔራዊ የትራንስፖርት ደህንነት ቦርድን ምክር በሥራ ላይ ያውላል፡፡ የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን የ2013 ለታቀደው የፌደራል 2012 ዓ.ም. 49 USC §5309 እና §5307 እና PRIIA ፕሮጀክቶች በጀት እና ለፌደራል የትራንስፖርት አስተዳደር

ለነዚህ ፕሮጀክቶች ያቀረባቸው ማመልከቻዎች ከታች ተጠቅሰዋል፡፡ የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን እነኝህን ፕሮግራሞች ለአካባቢው ብሔራዊ የመጓጓዣ ዕቅድ ቦርድ ለ2013-2018 ዓ.ም. ለዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ መሻሻል ፕሮግራም ለማቀረብ እቅድ አለው፡፡

**<u>የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን የ2013 የንብረት መሻሻል ፕሮግራም</u>**

የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን የ2013 የንብረት መሻሻል ፕሮግራም አጠቃላይ በጀት $904,098,281 እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ይህ የበጀት ግምት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ሲችል . የፕሮጀክቱ መጠን ግን ለውጥ አይኖረውም፡፡ ይህ የታቀደው ፕሮግራም በሚከተሉት የገንዘብ ምንጮች ይደገፋል፡- $139,365,000 ከ 49 USC §5307 መዋጮ, $35,206,124 ከኣካባቢው 49 USC §5307 በከፊል የሚሰጡ, $101,266,000 ከ49 USC §5309, $25,581,626 ከአካባቢው 49 USC §5309 በከፊል የሚሰጡ ምንጮች $150,000,000 ከፌደራል PRIIA የዕርዳታ ገንዘብ ምንጭ, $150,000,000 ከአካባቢው PRIIA በከፊል የሚሰጡ, $4,800,000 ከፌደራል የዓየር መተፋፈን ማቃለያ እና የዓየር ጥራት ፕሮገራም (CMAQ)፣ በግምት $112,680,000 ተጨማሪ ለአካባቢው ለመዋቅር ማሻሻያ ከተመደቡ ምንጮች እና ቀሪው $185,199,531 ከአለፈው ዓመት እና ከተለያዩ ምንጮች፡፡

የንብረት መሻሻል ፕሮግራሙ የሚከተሉትን የፕሮጀክት ክፍሎች ያካትታል:

ሀ. **ተሽከርካሪዎች/የተሽከርካሪ ዕቃዎች**. የአውቶቡስ መተኪያዎች እና ማደሻዎች፣ የባቡር መተኪያዎች እና ማደሻዎች፣ የባቡር ደህንነትና አስተማማኝነት፣ የሜትሮአክሰስ ተሽከርካሪ ደህንነትና አስተማማኝነት፣ የሜትሮአክሰስ ተሽከርካሪ መተኪያዎች እና የመተኪያ ዕቃዎች፣ የመከላከያ ጥገናን ያካትታል፡፡

ለ. **የባቡር ሀዲዶች ጥገና-** የሀዲድ መስመር ክፍሎችን ያካትከታል፡፡

ሐ. **የሕንፃዎች ጥገና**. የአውቶቡስ ጋራዥ እደሳ እና መተካት፣ የሀዲድ ቦታዎች እና ሕንፃዎች ማደስን ያጠቃልላል፡፡

መ. **መዋቅሮችእና ቴክኖሎጂ**. የኤሌክትሪክ ኃይል መዋቅሮችን ማሻሻያዎች፣ የእንቅስቃሴዎች ድጋፍ ሶፍተዌር፣ የአሠራር ድጋፍ ሶፍትዌር እና መሣሪያዎች እና የባቡር መሳፈሪያ መሣሪያዎችን ያካትታል፡፡

ሰ. **መንገድ እና አሠራር**. የመንገድ እደሳ፣ የጣቢያውና የመሿለኪያ የውሀ ፍሳሽ መከላከያን ያካትታል፡፡

ረ. **የተሳፋሪዎች ሕንፃዎች**. የኤሊቬተር እና የመወጣጫ ደረጃ፣ የጣቢያ እደሳን ያካትተካል፡፡

ሠ. **ሌሎች ማሻሻያዎች**. የጣቢያ ብቃት ፕሮጀክት እደገት፣ የባቡር ኮሪደሮች፣ ቢስኪሌት እና የእግረኛ መንገዶች መሻሻልን ያካትታል፡፡

ሸ. **የጥገና መሣሪያዎች**. የሀዲድ እና የአውቶቡስ ጥገና እና የሥራ ሕንፃዎችን ያካትታል፡፡

ቀ. **ሌሎች ሕንፃዎች**. የሥራ እና የተተኪ ፖሊሶች ሕንፃዎች፣

በ. **የፕሮጀክት አስተዳደር እና ድጋፍ**

ፕሮጀክቱ በሚካሄድበት ጊዜ ልዩ አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው፣ለአካለ ስንኩሎች እና ለአዛውንቶች አስፈላጊው ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡ ፕሮጀክቶቹ አጠቃላይ የዋሽንግተን አካባቢ የመሬት አጠቃቀም እና የመጓጓዣ ዕቅዶችን ይከተላል፡፡ በፕሮጀክቶቹ ምክንያት ምንም ዓይነት የአካባቢ ጉዳት ይመጣል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን በፌደራል መጓጓዣ አስተዳደር ድንጋጌ 49 CFR ክፍል 604 ለመጓጓዣ አገልግሎቶች በተፈቀደው መሠረት የአውቶቡስ ኮንትራት አገልግሎት ያካሂዳል። ኮንትራቱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚወጡ የአሠራር ወጭዎችን ለመሸፈን የመሳፈሪያ ዋጋዎችን በመተመን እራስ አገዝ ነው። አገልግሎቶቹ እና የክፍያ ዋጋዎቹ በዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን በውልና የተለየ የመጓጓዣ አገልግሎት ቀረጥ ቁጥር 17 ከመጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ.ም በሥራ ላይ ውሎ በቦርድ ውሳኔ 2008-56 ተሻሽሎ በህዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም. በሥራ ላይ የዋለው ፅሁፍ ላይ ሰፍረዋል። የቀረጥ እና የአውቶቡስ ውል የገንዘብ አደላደል ዕቅድ በዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን የአውቶቡስ አገልግሎት ክፍል ለሕዝብ ይፋ ነው።

**<u>ለምርመራ የቀረቡ ፅሁፎች</u>**

የ 2012 ዓ.ም. የታቀደው የዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን የንብረት መሻሻል ፕሮግራም በድረ ገጽ http://www.wmata.com/about_metro/docs/ProposedFY2013Budget.pdf ይመልከቱ። የ2013 ዓ.ም. የበጀት ዕቅድ እስከ መጋቢት 12 ቀን 2012 ዓ.ም. እስከ መሸቱ አስራ አንድ ሰዓት ከሰኞ እስከ ዐርብ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት እስከ ከቀትር በኋላ አስር ሰዓት በለው ጊዜ መደብ ውስጥ፣ ዓመት በዓላትን ሳይጨመር፣ በOffice of the Secretary, Washington Metropolitan Area Transit Authority, 600 Fifth Street, NW, Washington, D.C. 20001 ለሕዝብ ምርመራ ክፍት ነው።.

በ2013 ዓ.ም. የታቀደው የፕሮጀክት ፕሮግራም በዋሽንግተን አካባቢ የመጓጓዣ ባለሥልጣን የቦርድ ዲሬክተሮች ከመጽደቁ በፊት ካልተለወጠ በስተቀር የመጨረሻው የፕሮጀክት ፕሮግራም ነው።